የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር**

# የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የልዩ ስልጠና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር ---------/2017"

**ጥቅምት**/ 2017 **ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

<u>**መመሪያ ቁጥር** --------2017</u>

# የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የልዩ ሥልጠና አሰጣጥ መመሪያ

የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚደርሰው የትራፊክ አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ብዙዎችን ለህልፈተ ሕይወትና ለአካል ጉዳት እንዲሁም ለከፍተኛ የንብረት ውድመት እየዳረገ የሚገኝ ክስተት በመሆኑ፤

ለትራፊክ አደጋ መከሰት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነት ግን የአሽከሪካሪዎች ስህተት ከፍተኛውን ድርሻ ስለሚይዝ ልዩ ሥልጠና በመስጠት እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ ብቁ እንዲሆኑ በማድረግ አደጋውን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12(2) እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 6 (ለ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የልዩ ሥልጠና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር**--------/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "**ሚኒስቴር**" **ወይም** "**ሚኒስትር**" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡
2) "**አገልግሎት**" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 493/2014 መሠረት የተቋቋመው የመንገድ ደኅንነት እና የመድን ፈንድ አገልግሎት ነው፡፡
3) "**አሽከርካሪ**" ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሸ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክር ሰው ነው፡፡
4) "**ልዩ ሥልጠና**" ማለት በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 2(40) እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 8 (6) (ለ) መሠረት የሚሰጥ የሥልጠና ዓይነት ነው ፡፡
5) "**መደበኛ ሥልጠና**" ማለት በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 2(41) መሠረት የሚሰጥ የሥልጠና ዓይነት ነው፡፡
6) "**ሰርተፍኬት**" ማለት መደበኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሯቸው በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ ሥልጠና በመውሰድ የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በብቃት ለማሽከርከር እንዲችሉ የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ነው፡፡
7) " **የሥልጠና ሰነድ**" ማለት **ልዩ** ሥልጠና ለሚሰጣቸው አሽከርካሪዎች በተቀመጠው ርዕስ ላይ በሚኒስቴሩ የጸደቀ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፡፡
8) "**አሠልጣኝ**" ማለት በማሽከርከር ብቃት ሥልጠና ለመስጠት የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡
9) "**ማሠልጠኛ ተቋም**" ማለት በማሽከርከር ብቃት ሥልጠና ለመስጠት በሕግ እውቅና ያለው መንግሥታዊ ወይም የግል የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋም ማለት ነው፡፡
10) "**ቢሮ**" ማለት የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፡፡
11) "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰዉነት ችሎታ የተሰጠዉ ነው፤
12) በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ መመሪም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
13) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **ዓላማ**

የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የልዩ ሥልጠና በመስጠት እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ ብቁ እንዲሆኑ በማድረግ የሚደርሰውን የሞት፣ የከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት፣ እንዲሁም ከፍተኛ የንብረት ውድመትን መቀነስ ነው።

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች እና በሁሉም መንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሕዝብ እና በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሰመሩ አሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የልዩ ሥልጠና አሰጣጥ ድጋፍ ማዕቀፎች

5. **የልዩ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል የድጋፍ ማዕቀፍ**

   1) **የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ከሆኑና** መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን፡-

   ሀ) መመሪያው የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በሚያሽከረክሩ አሽከሪካሪዎች ላይ ወጥነት ባለው መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

   ለ) የመመሪያውን አተገባበር ውጤታማ ለማድረግ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

   ሐ) ሀገር አቀፍ የልዩ ሥልጠና ሰነዶች በአገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ያጸድቃል፤

   መ) የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በአገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፤

   ሠ) የመመሪያውን አፈጻጸም በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

2) **የመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ከሆኑና ማንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን፦**

ሀ) በመመሪያው አተገባበር ዙሪያ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል።

ለ) የሥልጠና ሰነድ በማዘጋጀት እንዲፀድቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥልጠና ሰነዱን ይዘት በመፈተሽ የማስተካከያ ሐሳብ ያቀርባል።

መ) አጠቃላይ ሥልጠናው ስለሚሰጥበት አግባብ የሥልጠና መርሀ-ግብር ያወጣል፤ በወጣው መርሀ-ግብር መሠረት መፈፀሙንም ይከታተላል።

ሠ) ልዩ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ሥልጠናውን የሚሰጡበትን መስፈርት ያዘጋጃል።

ረ) የልዩ ሥልጠና የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

ሰ) የልዩ ሥልጠና ሰርቲፊኬት ያዘጋጃል፤ ሥልጠናውን ለሚሰጡ አካላትም ያሰራጫል።

ሸ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥልጠና የወሰዱ ተቋማት መረጃን በአግባቡ ያደራጃል፤ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል።

ቀ) የልዩ ሥልጠናው አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በጣሱ አሠልጣኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

በ) ሥልጠናን ለመስጠት የተፈቀደላቸውን አካላት የፈቃድ ዕድሳት ጊዜን ይወስናል።

3) **የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ከሆኑና ማንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን፦**

በክልሉ ሕግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ተከታዮቹን ሥራዎች ያከናውናል።

ሀ) ይህን መመሪያ የመፈፀምና የማስፈፀም፤

ለ) በመመሪያ አተገባበር ላይ ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ፤

ሐ) የልዩ ሥልጠና የሚሰጡ አካላትን በወጣዉ ስታንዳርድ ወይም መስፈርት መሠረት በመለየት ለአገልግሎቱ የማሳወቅ፤

መ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታተመዉን የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለሰልጣኞች ይሰጣል፤

ሠ) የልዩ ሥልጠና የሚሰጡ አካላትን በመስፈርቱ መሰረት መለየት እና ለአገልግሎቱ ያሳውቃሉ

ረ) የሥልጠናዉን አፈጻጸም ለመከታተል በየደረጃዉ ባለዉ መዋቅር የድጋፍ፤ ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያከናዉናል፤

ሰ) በክትትልና ቁጥጥር የተገኙትን የአፈፃፀም መረጃዎች ለአገልግሎቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፤

4) **የትራፊክ ፖሊስ**

1) ማንኛውም የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሸከርካሪ አሽከርካሪ እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሸከርካሪ አሽከርካሪ የልዩ ሥልጠና ሰርተፊኬት መያዙን ይቆጣጠራል፤
2) የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ያልያዘ አሽከርካሪ ከተገኘ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሠረት እርምጃ ይወስዳል።

## ክፍል ሦስት

## ግዴታዎች

### 6. የልዩ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ግዴታዎች

ልዩ ሥልጠና ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል።

1) የልዩ ሥልጠና የሚወስዱ አሽከርካሪዎችን ስም ዝርዝር፤ የሥልጠና መርሀ-ግብር ለአገልግሎቱ የማሳወቅ፤
2) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ልዩ ሥልጠና መስጠት የሚያስችል የሙያ ፈቃድ የመያዝ፤
3) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የልዩ ሥልጠና ሰነድ መሠረት የልዩ ሥልጠና መስጠት፤

### 7. የተሸከርካሪው ባለቤት ግዴታዎች

ማንኛውም የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሸከርካሪ ባለቤት የሚቀጥረው አሽከርካሪ መደበኛ የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መኖሩን ከማረጋገጥ ባሻገር ተከታዮቹ ግዴታዎች አሉበት።

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀጥራቸው አሽከርካሪዎች ህጋዊ የልዩ ስልጠና ሰርተፊኬት መኖሩን ወይም መያዙን የማረጋገጥ፤
2) ይህ መመሪያ ከመዘርጋቱ በፊት ቀድሞ የተቀጠረ አሽከርካሪ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሰረት ልዩ ስልጠና እንዲወስድ የማድረግ፤
3) ለአሽከርካሪዎች ልዩ ስልጠና በሚሰጣቸው ጊዜ የማስተባበር፤ የመከታተል እና የመደገፍ፤
4) በማህበሩ ሥር የሚገኙ አሽከሪካሪዎች በወቅቱ ልዩ ሥልጠና እንዲያገኙ የማስተባበር፤

### 8. የአሽከርካሪዎች ግዴታዎች

ማንኛውም የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት።

1) ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱ በሚያወጣው መርሀ-ግብር መሠረት ልዩ ሥልጠናውን የመውሰድ፤
2) የሕዝብ ወይም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለማስከርከር ቅጥር ሲፈጽም ለቀጣሪው አካል የልዩ ሥልጠና ሰርተፊኬት የማሳየት፤
3) በሚያሽከረክርበት በማንኛውም ወቅት የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ይዞ የመገኘት፤
4) የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት እንዲያሳይ በትራፊክ ፖሊስ ወይም በትራንስፖርት ተቆጣጣሪ በሚጠየቅበት ወቅት የልዩ ሥልጠና ሰርተፊኬት የማሳየት፤
5) ልዩ ሥልጠና ለመውሰድ ወደ ማሠልተኛ ተቋም በሚሄድበት ጊዜ ሕጋዊ እና የታደሰ መንጃ ፈቃድ ይዞ የመገኘት፤
6) ሥልጠናውን ከመውሰዱ በፊት ማሟላት የሚገባውን አስገዳጅ ሁኔታዎችን በመፈጸም ሕጋዊ ደረሰኝ ይዞ የመቅረብ ወይም ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የመገኘት፤
7) የልዩ ሥልጠና ፈቃድ ሰርተፍኬት የማደሻ ጊዜውን ጠብቆ የማሳደስ፤
8) የሚሰጠውን የልዩ ሥልጠና ፈተና የማለፍ፤

## ክፍል አራት

## ስለ ልዩ ሥልጠና ይዘትና ሥልጠናው ስለሚሰጥበት አግባብ

### 9. የልዩ ሥልጠና ሰነድ ይዘት

1) የመንገድ ትራፊክ አደጋ ነባራዊ ሁኔታዎች፤
2) የመንገድ ትራፊክ አደጋ መንስኤዎች እና መከላከያ መንገዶች፤
3) የትራፊክ አደጋ ጉዳት ከባድ እንዲሆን የሚያደርጉ ምክንያቶች፤
4) የማሽከርከር ሥነ- ልቦና እና ሥነ- ባህሪ፤
5) ሙያዊ ሥነ-ምግባር እና የደንበኛ አያያዝ፤
6) የመልካም አሽከርካሪ ባህርያትን ለማዳበር የሚጠቅሙ አካላዊ እና ሥነ- ልቦናዊ እውነታዎች፤
7) አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከር፤
8) የፍጥነት መንገድ አነዳድ፣
9) የደረቅ ጭነት አጫጫንና አወራረድ፤ የህዝብ ትራንስፖርት አጫጫንና አወራረድ ወዘተ
10) የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ፤
11) ልዩ ሥልጠና የሚሰጥበት መንገድ በፓወር ፖይንት፣ የቡድን ውይይት በማድረግ፣ አስታማሪ በሆኑ ቪዲዮዎች፣ በፎቶ ግራፎች እና መሰል የማስተማሪያ ዘዴዎች ይሆናል።

### 10. ልዩ ሥልጠናውን የሚሰጡ አካላት

ልዩ ሥልጠናውን የሚሰጡት አገልግሎቱ በሚያወጣው የልዩ ሥልጠና መስጫ መመዘኛ መስፈርት መሠረት ልዩ ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት ይሆናሉ።

### 11. ልዩ ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ የሚሰጣቸው አካላት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

1) በዘርፉ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው፤
2) ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ልዩ ሥልጠና ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው፤
3) ለሥልጠና ምቹ የሆነ የሥልጠና ክፍል እና ቁሳቁሶችን የሚያሟላ፤

### 12. ልዩ ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ የሚሰጣቸው ተቋማት ግዴታዎች

ልዩ ሥልጠናውን ለመስጠት የሚያስችል የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል።

1) አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት ልዩ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ፈቃድ የመያዝ፤
2) የልዩ ሥልጠና ሰጪነት ፈቃድ በየዓመቱ የማሳደስ፤
3) በየጊዜው ሥልጠና የሚሰጣቸውን አሽከርካሪዎች ብዛትና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለፈቃድ ሰጪው ሪፖርት የማድረግ፤
4) ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ልዩ ሥልጠናውን መስጠት ካቆመ ወይም የተቀመጡትን ግዴታዎች መወጣት ካልቻለ ለፈቃድ ሰጪው አካል ፍቃዱን የመመለስ፤

### 13. ስለ ሥልጠና ጊዜ

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ሥልጠናውን ሲወስድ በቀን 3 ሰዓት ሆኖ ለአምስት ቀን 15 ሰዓታት በክፍሉ ውስጥ ተገኝቶ ልዩ ሥልጠና መውሰድ አለበት።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በየሁለት ዓመቱ በቀን 2 ሰዓት ሆኖ ለአምስት ቀናት 10 ሰዓት ልዩ ሥልጠናውን ወስዶ ፈቃዱን ያሳድሳል።

### 14. ስለ ሥልጠና ወጪ

የሕዝብ ወይም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች አገልግሎቱ በሚያወጣው የታሪፍ ስሌት መሠረት በራሱ በሰልጣኙ የሚሸፈን ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 15. ክልከላ

1) በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም  የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ልዩ ሥልጠና ሳይወስድና ሰርተፊኬት ሳይዝ ማሽከርከር የተከለከለ ነው።
2) ማንኛዉም የተሽከሪካሪ ባለቤት ተሽከርካሪውን ልዩ ሥልጠና ያልወሰደና ልዩ ሥልጠናውን ስለ መውሰዱ የሚያረጋግጥ ሰርቲፊኬት ያልያዘ አሽከሪካሪ እንዲያሽከረክር መፍቀድ የለበትም።
3) የተሰጠውን የልዩ  ሥልጠና ፈቃድ ከምድቡ ውጪ መጠቀም አይችልም።
4) ልዩ ሥልጠና ለማሠልጠን የሚያስችል ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ፈቃዱን ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው።

## 16. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1) የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ሳይኖረው ወይም የተሰጠዉን የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬትከምድቡ ውጪ ተሽከሪካሪን ያሽከረከረ አሽከሪካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ  መሠረት መንጃ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ የሚቀጣ ሲሆን መደበኛ መንጃ ፈቃዱ ለ 6 ወር ይታገዳል።
2) የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ኖሮት ሳይዝ  ተሽከሪካሪን ያሽከረከረ አሽከሪካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ ይቀጣል።
3) የልዩ ሥልጠና ሰርተፍኬት ለሌለዉ አሽከሪካሪ ተሽከሪካሪውን እንዲያሽከረክር የፈቀደ ወይም አሳልፎ የሰጠ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ  መሠረት የሚቀጣ ሲሆን ተሽከሪካሪው ከማንኛዉም አገልግሎት ለ 3 ወራት  ይታገዳል።
4) በዚህ መመሪያ መሠረት ኃላፊነት የተጣለበት ማንኛውም አሰልጣኝ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ይታገዳል፤ ከ3ኛ ጊዜ በላይ ከሆነ የሙያ ፈቀዱ ይሰረዛል።
5) በዚህ መመሪያ መሠረት ኃላፊነት የተጣለበት ማንኛውም የማሠልጠኛ ተቋም የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ለ6 ወር ይታገዳል፤ ከ3ኛ ጊዜ በላይ ከሆነ የሥልጠና ፈቀዱ ይሰረዛል።

## 17. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

1) ማንኛውም ቅሬታ ያደረበት ግለሰብ ወይም ተቋም ቅሬታው በተፈጠረ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቢሮ ማቅረብ ይችላል።

2) ቢሮው ቅሬታው በቀረበ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት።
3) ቢሮው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግለሰብ ወይም ተቋም ውሳኔው በተሰጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬተውን ለትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ያቀርባል።
4) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ቅሬታው በቀረበ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ውሳኔውን ያሳውቃል።
5) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል።

18. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

19. **መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር)

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚንስትር

**አባሪ** 1

**የሕዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎችየ የልዩ ሥልጠና ማረጋጫ ምስክር ወረቀት**

የፈቃድ ሰጪ ስም-------------------------

የአሽከርካሪ ሙሉ ስም _______________________________ ፎቶ

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ደረጃ፡-______________

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር፡-_____________

የምስክር ወረቀት ቁጥር _____________________________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን ______________________

የምስክር ወረቀቱ አገልግሎት የሚያበቃበት ጊዜ___________

ፈቃድ ሰጪ አካል ፊርማ_________________